22 ዓመት ቁጥር131 አሶሳ
21/ 2008 ዓ.ም

22th year 131
assosa 21/ 2008 ዓ.ም

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
## ልሣነ ህግ ጋዜጣ

-

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ
መንግስት ምክር ቤት

ጠባቂነት የወጣ አዋጅ

**አዋጅ ቁጥር 131/2008ዓ/ም**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ስልጣንና ተግባራቸዉን እንደገና ለመወሰን የወጣአዋጅ ቁጥር131/2008 ዓ/ም**

የክልሉንየመንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር94/2003ዓ/ምማሻሻል በማስፈለጉ፤

በክልሉየመንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ወሰን የሆነዉን የሕዝብና የመንግስት ሀብት ቁጥብ በሆነ አኳኃን ለማጠቀም በሚያስችል የተቀናጀ አስተዳደር እና አገልግሎት በማስጠት ለዘላቂ ልማት እና መልካም አስተዳደር ማስፈን ብሎም ደህነትን ለማጥፋት የላቀ ድርሻ እንዳለው በማንዘብ፤

በአደረጃጀትና በአሠራር የታዩ ችግሮችን ግምት ወስጥ በማስገባት የክልሉን ድርጅታዊ መዋቅርና አሠራር በጥናት ሜተሸና የማሻሻያ እርምጃ መወሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዐስ ቁጥር 3.1መሠረት የሚከተለው ታወጇል፡፡

የአንዱ ዋጋ -------
-

Unit Price

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ"*የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር* 1312008 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## አንቀጽ 2

## ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡ -

1. **"የክልሉ ም/ቤት"** ማለት በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 (1) መሠረት የተቋቋመዉ አካል ነው፤

2. **"ህገ -መንግስት"** ማለት የተሻሻለው የ1995 ዓ/ም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት ነው፤

3. **"የማስተዳድር ምክር ቤት"** ማለት የክልሉ የህግ አስፈጻሚ አካል የሆነው የክልል ማስተዳድር ም/ቤት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የተዋረድ አስፈጻሚ አካላት ሊጨምር ይችላል፤

4. **"ቢሮ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ከፍተኛ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እና እንደነገሩ ሁኔታ ሌሎች ማሥሂያ ቤቶችን በበላይነት የሚዋሩ ነው፤

5. **"ሌሎች ማሥሂያ ቤቶች"** ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች መሠረት የተቋቋሙ ወይም የሚቋቋሙ ጽህፈት ቤቶችን፣ ኮሚሽኖችን፣ ባለሥልጣኖችን፣ ተቋማትንና ሌሎች መሰል አስፈጻሚ አካላትን ይጨምራል::

## ክፍል ሁለት

## ስለአስፈፃሚ አካላት ማስሪያ ቤቶች

## አንቀጽ 3

## መቋቋም

1. የሚከተሉት የአስፈፃሚ አካላት ማስሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፤

(ሀ) የሰው ሀብት ልማትና ፐብሊክ ሰርቪስቢሮ

(ለ) ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

(ሐ) የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ

(መ) የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ

(ሠ) የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ

(ረ) የባህልናቱሪዝምቢሮ

(ሰ) ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

(ሸ) የወጣቶች እና ስፖርትቢሮ

(ቀ) የወሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ

(በ) የጤናጥበቃ ቢሮ

(ተ) የፍትህቢሮ

(ቸ) የትምህርትቢሮ

(ኀ) የሴቶች እና ሕፃናትጉዳይቢሮ

(ነ) የመንግሥትኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ

(ኘ) የአካባቢ፣ ደንናሜት አስተዳደር ቢሮ

(አ) የገቢዎችባለሥልጣን

(ከ) የቴክኒክ ሞያና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቢሮ

2. በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ 1 ስር የተዘረዘሩትየአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ተጠሪነት ለክልሉ መንግሥት ማስተዳደር ምክር ቤትና ለርዕሰ ማስተዳደሩ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4

## ስለሌሎች የአስፈጻሚ አካላት ማስሪያ ቤቶች

1. በዚህ አዋጅ ወስጥ ያልተማከቱ ሌሎች የክልሉማግሥትአስፈጻሚአካላት በሚቋቋሚ ሕጎቻቸው ማረት ስራቸወን ይቀጥላሉ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ ያሉና ወደፊት የሚቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትን በሚማከት በማተዳደር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለርዕሰማተዳደሩ፣ ምክትል ርዕሰ ማተዳደሩ እና ማተዳደር ምክር ቤት

## አንቀጽ 5

## ማተዳደርምክር ቤት

1. የሚከተሉትየማተዳደርምክር ቤት አባላት ናቸው፤
   (ሀ) ርዕሰ ማተዳደር

   (ለ) ምክትል ርዕሰ ማተዳደር

   (ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ1 ስርየተዘረዘሩት አስፈጻሚ አካላትን የሚሙ ኃላፊዎች፤ እና

   (መ) በርዕሰ ማተዳደሩ የሚሾሙ ሌሎች ኃላፊዎች፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የተማከተው ማንኛወም ኃላፊ በማተዳደር ምክር ቤቱ ስብሰባ የማኘት ግዴታ አለበት፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማኘት በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ካንድ በላይ ምክትሎች ባሉ ጊዜ፤ በግልፅ ተለይቶ በፅሁፍ ወክልና የተሠጠው ምክትል ኃላፊ ወይም በግልፅ ተለይቶ በፅሁፍ ወክልና የተሠጠው ከሌለ በሹመት ቅደሚ ያለው ምክትል ኃላፊ በማተዳደር ምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይገኛል፡፡

## አንቀጽ 6

## የክልሉ ርዕሰ ማተዳደር ስልጣንና ተግባር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ማንግስት ርዕሰ ማተዳደር ሥልጣንና ተግባር በሕገ ማንግስቱ አንቀጽ 61 እና በሌሎች ህጎች ተለይተወየተማከቱት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 7

## የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስትምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 62 እና በሌሎች ህጎች ተለይተውየተመለከቱት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 8

የክልል መስተዳደር ም/ቤት ስልጣንና ተግባር

ስልጣንና ተግባሩ በተሻሻለዉ የክልሉ ህገመንግስት አንቀጽ 59 እና በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 9

## የመስተዳድር ምክር ቤት አሰራር

1. የመስተዳድር ምክር ቤት ፡-

(ሀ)የራሱየዉስጥደንብይኖረዋል፤

(ለ) በዉስጥደንቡበሚወሰነ ወመሠረትመደበኛናአስቸኳይስብሰባዎችያደርጋል፤

(ሐ) ምልአተጉባኤየሚሟወከአባላቱከግማሽበላይሲገኙይሆናል፤

(መ) የሚያስተላልፈዉዉሳኔበተባበረድምጽይሆናል፤በተባበረድምጽመወሰንካልተቻለበድምጽ

ብልጫይወሰናል፡፡

2. ርዕሰመስተዳድሩ፡-

(ሀ) የመስተዳድር ምክርቤትአባላትአጀንዳየማስያዝመብታቸዉእንደተጠበቀሆኖ፣ለምክርቤቱ

በአጀንዳየሚቀርበጉዳዮችንይወስናል፤

(ለ) የመስተዳድር ምክርቤቱንስብሰባይመራል፤

(ሐ) ለመስተዳድር ምክርቤቱበአጀንዳየቀረበጉዳይበርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት መታየት

የሚያስፈልገዉሆኖካገኘዉአጀንዳዉን ለሌላ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 10

## የርዕሰመስተዳድርጽህፈት ቤት

1. የርዕሰ ማስተዳደር ጽህፈት ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 63 መሠረት የርዕሰ ማስተዳደር እናየማስተዳደር ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

2. በዚህአንቀፅንዑስአንቀፅ 1 ላይ የተጠቀሰዉእንደተጠበቀሆኖ ርዕስ ማስተዳደሩ ስልጣንና ተግባሩን ለማከናወን የሚረዱ ልዩ ልዩ ጽህፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት

## የአስፈፃሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች ሥልጣንናተግባር

### አንቀጽ 11

### የወልስልጣንናተግባር

1. በዚህአዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የማስተዳደርምክር ቤት አባል የሆነ እያንዳንዱ የአስፈፃሚ አካል ማሥሪያ ቤት በሥሪው ማስክ፡-

(ሀ) ሕግና ፖሊሲዎች ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያወላል፤

(ለ) ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ሚጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያሰራጫል፤

(ሐ) የፌደራልና የክልሉ ሕጎች በስራ ላይ መዋላቸዉን ያረጋግጧል፤

(መ) በሕግ ማስረት ወሎችና ስምምነቶች ያደርጋል፣ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

(ሠ) የኤች አይ ቪ ኤድስ ተጠቂዎችና የአካል ጉዳተኞች እኩል ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ያመቻቻል፤

(ረ) በሚያዘጋጃቸዉፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማትፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችየሴቶችንና የወጣቶችንጉዳይ፣ የሕጻናት ጥቅምና ደህንነትን ያስጠብቃል፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የአደጋ ስጋትስራአሜራርን፣ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር ሜካተታቸዉን ያረጋግጧል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

(ሰ) ክልላዊ የለወጥና የሚልካምአስተዳደርስራዎችንይፈጽሚል፣ ያስፈጽሚል፣ ዉጤታማ ነታቸዉን ያረጋግጧል፡፡

2. በየአስተዳደርእርከንየሚገኙትንየአስፈፃሚአካላትማሥሪያቤቶችንእናበሚቋቋሚያ ሕጎቻቸዉተጠሪየሆኑ የአስፈፃሚአካላትማስሪያቤቶችንአፈጻጸምበበላይት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አደረጃጀታቸው፣ የሥራ ፕሮግራሞቻቸዉንና በጀታቸዉን መርምሮ ለሚመለከተዉየመንግስትአካልእንዲያቀርቡያደርጋል፤

3. ተጠሪው የሆኑ የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የልማቱ አጋዥ ሆነው ማከራታቸውን ያረጋግጣል፤

4. በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

5. ስለሥራው አፈፃፀም በየወቅቱ ለርዕሰ ማስተዳደሩ እና ለማስተዳደር ምክር ቤት ሪፓርት ያቀርባል፡፡□

## አንቀጽ 12

## የቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ተጠሪነት

1. በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩት የማስተዳድር ም/ቤት(ካቢኔ) አባላት በክልል ማስተዳድር ምክር ቤት(ካቢኔ) ለሚያሳልፉት ወሳኔ የጋራ ኃላፊነትና ተጠሪነት አለባቸው፤

2. በዚህአንቀጽንዐስ አንቀጽ 1 የሠፈረው ድንጋጌእንደተጠበቀሆኖ እያንዳንዱ መ/ቤትየተቋቋመብትን ዓላማ መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ተለይተወየተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ስልጣንና ተግባራት

## አንቀጽ 13

## የሰዉ ሀብት ልማትና ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ

ቢሮወየሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በፌደራል የሚወጡ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ፈጻሚ ባለቤት እንዲኖራቸው በማድረግ አቀናጅቶ በበላይነት ይመራል፣ ለተግባራዊነታቸው የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

2. በክልሉ የልማት መሪሃ ግብር የሚከተቱ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ይከታተላል፣ በበላይነት ያስፈጽማል፣ወጤታማነታቸወንና ወስንነታቸወን ይገመግማል፣የሚሻሻሉበትንም አማራጭ ያቀርባል፤

3. በክልሉ መንግስት የሚነደፉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት እቅዶችን መነሻ በማድረግ አጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የሚጠይቁትን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት፣ የአሠራር ሥርዓትና ሌሎች የአቅም ግንባታ ፍላጎቶች ላይ ጥናት በማድረግ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ፖሊሲ ነክና ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ሀሳብ ያመነጫል፤

4. በፌደራል ደረጃ ተቀርጸው በሥራ ላይ የሚውሉ የተለያዩ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የሥልጠና ፕሮግራሞች በክልሉ በተገቢው አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

5. በክልሉ የተዋቀሩ አስፈጻሚ አካላት አንድ ወጥ የሆነ፣ ተደጋጋፊና የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት፣ የመረጃ አያያዝ፣ ልወውጥና አጠቃቀም፣ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዲኖር ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

6. የአቅም ግንባታ ሥራን ለማጐልበት የሚያስችሉ ተቋማት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ በአቅም ግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን ይገመግማል፣ ወጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን ስልት ይቀይሳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ፕሮግራሞች እንዲነደፉ ያደርጋል፤

7. የግልና የሕዝብ ተቋማትን፣ የማህበራትንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፤

8. ተጠሪነታቸዉ ለቢሮዉ የሆኑ መ/ቤቶች የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የተሻሻሉ የአሠራር ሥርዓቶች እንዲሁም ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በማየት አስፈላጊወን እገዛ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፤

9. የመንግስት መ/ቤቶችን የሚጸምና የማስፈጸም አቅም የሚያድግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ለዚህም ተገቢወን እገዛ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

10. ሥራ ላይ የዋሉ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ለመተግበር ከፌደራል መንግስት ማለል ተቋማትና ከሌሎች ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣ በጋራ በማናኘትም ፕሮግራሞቹ የበለጠ የሚዳብሩበትን፣ የሚሻሻሉበትንና በክልሉ የሚፈረወን ግንዛቤ የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

11. በክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት መሠረት የተለያዩ የሀገር ወስጥ እና ውጭ ሀገር የትምህርትና ሥልጠና እድሎች በአግባቡ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

12. የክልሉን መንግስት ማስሪያቤቶችበልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ ያሰዉ ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትና ጥቅም ላይ የሚዉልበት ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራይነቱን ይከታተላል፤

13. የሚጃና ማናኛ ቴክኖሎጂ በክልሉ ያስፋፋል፣ በልማት ላይ እንዲወሉ ያደርጋል፤

14. በክልሉ ለዲሞክራሲ ሥርዓትና ለሚልካም አስተዳደር ግንባታ እገዛ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ለተግባራዊነታቸዉ ያስተባብራል፤

15. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች አስተዳደርን በሚመለከት የወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች በስራ ላይ መዋላቸወን ይቆጣጠራል፤

16. የፌደራል የሰዉ ሀብት ልማትና ፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር በሚያወጣቸዉ የስራ ምዘናና ደረጃ ማስረት በክልሉ የመንግስት መ/ቤቶች ወስጥ በሚገኙ የሥራ መደቦች ላይ ምደባ ይሰጣል፤

17. ለመንግስት ሠራተኞች የተፈቀደወን የደመወዝ እስኬል፣ የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን በሚመለከት በሥራ ላይ እንዲወሉ ያደርጋል፤

18. በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ ደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ ዝወዉር እና የዲሲፕሊን ጉዳዮች በህጉ መሠረት ሚጸማቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ያረጋግጣል፤

19. የክልል ማስተዳደሩን የመንግስት ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል፣ ስታትስቲካዊ ሚጃዎች ያጠናቅራል፣ ለፌደራል የሰዉ ሀብት ልማትና ፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፤

20. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ አገልግሎታቸው እንዲራዘም ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚጨረሻ ወሳኔ ይሰጣል፤

21. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች ከሥራ ለማስናበት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የሚጨረሻ ወሳኔ ይሰጣል፤

22. ከክልሉ መንግስት ሠራተኞች ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎች ላይ የሚጨረሻ ወሳኔ ይሰጣል፤ያልተፈጸሙ የሲቪል ሰርቫንት የይግባኝ ቅሬታዎችን ለመደበኛ ፍርድቤቶችያስተላልፋል፤

23. ለክልሉ መንግስት ሠራተኞች የሥራ ወጤቶች መመዘኛመመሪያ ያወጣል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

24. በክልሉ መንግስት መ/ቤቶች የሚፈረጉ የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥርን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

25. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች የፌደራል ህጎችን በመተርጎም ረገድ ያጋጠሙ ችግሮችን ለፌደራል የሰዉ ሀብት ልማትና ፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፣ በትክክለኛ ትርጓሜቸዉ መሠረት መተግበራቸዉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

26. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልል መንግስቱን አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም በማምገም የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፣ሲፈቀድም ሥራና ሠራተኛ ማገናኘቱን ያረጋግጣል፤

27. በመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ የማስፈጸሚያ ሕጎች፣ በተቀናጀ መንገድ የሚተገበሩበትን ስልት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

28. የክልሉ መ/ቤቶች በስትራቴጂያዊ አመራር ዘይቤ የሚመሩበትንና የተቀናጀ የማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም ስልት የሚዳብርበትን ሥርዓት በመቀየስ ተግባራዊ መደረጋቸዉን ይከታተላል፤

29. ልማታዊ ሚልካም አስተዳደርለሚረጋገጥ መንግስት፣ህዝብንና ልማታዊ ባለሀብቱን አቀናጅቶ በሰራዊት አግባብ ያስተባብራል፤

30. የለዉጥ ፕሮግራሞች፣ ጥናቶችና ወጤቶችን አፈጻጸም በወቅቱ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያቀርባል፣ እንዲሁም በክልሉ አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የማሻሻያ ጥናቶችን በማየት የጥናት አፈጻጸም ቅደም ተከተል ያወጣል፣ ሚጃወንም በሥርዓት አደራጅቶ ይይዛል፤

31. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ረገድ የአገር ወስጥና የወጭ ተሞክሮዎችን በማጥናት ጠቃሚ ልምዶች ከክልሉ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

32. አላማዉን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## አንቀጽ 14

## የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱን የገጠር ልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ስልቶች በክልሉ ወስጥ ያስፈጽሚል፣ ይህንኑ መሠረት አድርጐ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል ሲፈቀድቅም በሥራ ላይ እንዲወል ያደርጋል፤
2. ከአስገዳጅ ወይም ህግ ከወጣላቸዉ የግብርና ምርቶች የግብይት ሥርዓት ዉጭ ለሆኑት ግብይቶች የህግ ሜቀሮችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማስደግ ከምርምርና ከማሰልጠኛ ሜከላት ጋር ተቀናጅቶና ተሳስሮ ይሰራል፣ ድጋፍም ይሰጣል፤
4. የግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ሞያዊ እገዛና ክትትል ያደርጋል፤ የግብርና ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
5. ተዛማች የሰብልና የእንስሳት በሽታ እንዲሁም ነባር የፀረ- ሰብል ተባይ ወረርሽኝ ሲነሳ አስቸኳይ የመከላከል ዕቅድ በማውጣት በክልሉ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችን እንዲሁም የኅብረተሰቡን አቅም በማስተባበር በባህላዊና ዘመናዊ መንገድ አደጋውን ይከላከላል፤
6. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን ለተጠቃሚዉ ህዝብ ለማሰረጽ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ምርታማነት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
7. የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ደንቦችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር በመተባባር ለግብርናና ገጠር ልማት መጣኑ አስፈላጊ የሆኑ የእርሻ መሣርያዎች፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች፣የእንስሳት መድሃኒት፣ የብድር አገልግሎት እና ሌሎች የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችአገልግሎት እንዲዳረስ ጥረት ያደርጋል፤
9. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በአካባቢ ላይ የሚያስከትለዉን ጉዳት ለመቆጣጠር የአፈርና የወሃ ጥበቃ ሥራ ስልትን እየቀየሰ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
10. በክልሉ ወስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉ የእንስሳት መድኃኒት፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፣በተገቢው መንገድም ስለመያዛቸው ይቆጣጠራል፤
11. በክልሉ ወስጥ ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳትና የአሳ ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል ድጋፍ ይሰጣል፣ ያበረታታል፤
12. የሠብል፣ የእንስሳትና የእስሳት ተዋጽኦ ምርትና ምርታማነት እንድያድግ ሞያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ ምቹ ሁኔታን ያመቻቻል፤
13. ቢሮው በሥሩ ለሚገኙ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ሜከላት፣ ዕፅዋት ክሊኒክ፣ የገጠር ቴክኖሎጂ ሜከል፣ አፈር ምርምርና እንስሳት ላብራቶሪዎችንና ሜከላትን ለግብርናው ዘርፍ አገልግሎት ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
14. የክልሉ የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ እንዲጠበቅ የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ስልት ቀይሶ ይሰራል፤

15. የነባር ብሔረሰብ ግብርና ዘይቤ በማጥናት የተፈጥሮ ሀብቱን አጠብበቅና ምርታማነትን ባገናዘበ ሜኩ የግብርና ዘዴ ስልት በመቀየስ ብሔረሰቦች ከዘመናዊው የግብርና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

16. አነስተኛ የመስኖ ልማዖች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

17. በቢሮዉ ስር ላሉ አስፈፃሚ አካላትና የልማት ተቋማትን በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፣ በተዋረድ ለዞንና ለወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት መ/ቤቶች ሙያዊ ድጋፍና እገዛ ይሰጣል፤

18. አደገኛና ማጤ አረሞች፣ በሽታዎችና ተባዮች ወደ ክልሉ እንዳይገቡ ተገቢዉን የመከላከያ ስልት ይነድፋል፣ተግባራዊ ያደርጋል፤በክልሉ ወስጥ የማገኙትንም እንዲወገዱ ጥረት ያደርጋል፣ከሚመለከታቸዉ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ያስተባብራል፤

19. የግብርናና ገጠር ልማትን ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፤

20. ዓላማውንለማስፈጸምየ ማቻሉሌሎችተዛማጅተግባራትንያከናወናል፡፡

## <u>አንቀጽ 15</u>

## <u>የንግድ፣ ኢንዱስትሪናትራንስፖርትቢሮ</u>

ቢሮዉምከተሉት ሥልጣንናተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤
2. በክልሉ ወስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፉ የግብይት ሥርዓትና ተገቢ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፤
3. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የንግድ ምዝገባናፈቃድአገልግሎትይሰጣል፣ይቆጣጠራል፣ይሰርዛል፣የንግድመዝገብየደራጃል፤
4. ተገቢያልሆነየንግድአሰራርንለመከላከልየሚያስችልየተሟሏሥርዓትይዘረጋል፣የንግድሕጎችመከበራቸዉንያረጋግጣል፣አፈፃፀማቸዉንይከታተላል፤
5. በሕግመሰረትለሸማቾችጥበቃያደርጋል፣የንግድእቃዎችንናአገልግሎቶችንሥርጭትይቆጣጠራል፤
6. አግባብ ባለው አካል የዋጋ ቁጥጥር የተደረገባቸዉን መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መተግበራቸዉን ይቆጣጠራል፤
7. አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃያላቸወየንግድዕቃዎችናአገልግሎቶችየደረጃወንመስፈርትማሟላታቸዉንይቆጣጠራል፤ከተዘጋጀላቸወደረጃበታችሆነ ወብተገኝትላይእርምጃይወስዳል፤
8. የሀገሪቱንሕጋዊሥነልክሥርዓትበአግባቡመተግበሩንይቆጣጠራል፤
9. የንግድና የዘርፍ የሙያ ማህበራትእንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤
10. የግብይትሥርዓትን በበላይነት ይመራል፣ የገበያ መሠረተ ልማት ያስፋፋል፣ የምርት ጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፣ የብቃት ሚረጋገጫ ይሠጣል፣ይከታተላል፣ በሕግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤

31. ዓላማውን ለማስፈጸም ማቻሉሌሎችተዛማጅተግባራትንያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 16

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽንቢሮ

ቢሮው ሚከተሉት ሥልጣንናተግባራት ይኖሩታል፡ -

1. የከተማኘየገጠርትስስር እና የከተሞችየእርስበርስትስስርእንዲጠናከርስትራቴጂይቀይሳልተግባራዊያደርጋል፤
2. አግባብ ባለው ሕግ የክልሉን የከተማ ሜት አስተዳደር ሥርዓትን ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣የከተማ ሜት አቅርቦትና አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤
3. የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራምን በባለቤትነ ትያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸውምአካላትጋርበመቀናጀትይደግፋል፣ አፈጻጸማንምይከታተላል፣ ዘላቂነ ትካለው የልማትተግባርጋርምያስተሳስራል፤
4. የከተሞችንየደረጃመመዘኛናደረጃ ይወስናል፣ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
5. ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤
6. የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት እና ከደህነ ት ቅነሳ ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፣ አፈጻፀማ ይከታተላል፤
7. በከተሞች ዘመናዊ ማስረተ-ልማት እንዲስፋፉ ጥረት ያደርጋል፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ ሜት ያዘጋጃል፤
8. የክልሉንከተሞች ፕላን ያዘጋጃል፣ አተገባበራቸውን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፤
9. በከተማ ፕላን ዝግጅት ለሚሰማሩ አማካሪዎች የብቃት ሚረጋገጫ ይሰጣል ደረጃቸውን ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፤
10. ከተሞች የሚያመነጩትን ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች የሚወገደበትንና ወበት ያላቸው የመናፈሻ አገልግሎቶች የሚስረቱበትን የአሰራርሥርዓት ይዘረጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤
11. በከተሞችለሕዝብ ልማት ሲባል ለመንግስታዊ ፕሮጀክቶችና ለሌሎች አገልግሎቶች ለሚውሉ ይዞታዎችና ከይዞታቸው ለሚነሩቀሉ ሰዎች ካሳ የሚከፈልበትሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል አፈፃፀማ ይከታተላል፤
12. ለተለያዩአገልግሎቶችየሚውልየለማሜትያዘጋጃል፣ለተገልጋይያቀርባል፣የአቅርቦቱንፍትሐዊነ ትያረጋግጣል፤የተላለ ፈሜትህጋዊነ ቱንተከትሉለልማትመዋሉንይከታተላል፣ህገ -ወጥግንባታዎችንይቆጣጠራል፣ህጋዊሥርዓትንያስይዛል፤
13. የሜትናየንብረትዋስትናካሳሥርዓትይዘረጋል፤
14. በቴክኖሎጂ የተደገፈና ወጥ የሆነ የከተማ ሜት ይዞታ ምዝገባና የአድራሻ ሚጃ ሥርዓት በክልሉ ይዘረጋል፤
15. በከተሞች የልማትና ሜልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ ነዋሪው ህዝብ በተደራጀ አግባብ እንዲሳተፍ ለማስቻል የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፣ የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤ ያስተባብራል፣ አፈጻጸማ ይከታተላል፤

16. በክልሉ የሚከሄደውን የቤቶች ልማት ፕሮግራሞችን ይመራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ የመኖሪያ ቤት እንዲሰራ ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

17. የፌደራልናየክልሉመንግስትየግንባታኮዶች፣ስታንደርዶችናሕጐችመከበራቸውንያረጋግጣል፣የዲዛይንናየግንባታሥራዎችንደረጃይወሰናል፤

18. በግንባታዘርፍለሚሰሙዩየምህንድስናባለሙያዎች፣አማካሪዎችናሥራተቋራጮችይመዘግባል፣የሙያሚጋገጫምስክርወረቀትይሰጣል፣ያድሳል፣ይሰርዛል፤

19. በክልሉመንግስትለሚገነቡሕንፃዎች የዲዛይንናየግንባታወሎችስለሚዘጋቸውየወልቃሎችናየቴክኒክመሜያያዘጋጃል፣በተገባወወልመሠረትየጥራትደረጃቸው፣የጊዜናየዋጋገደቦችተጠበቀውመስራታቸውንይቆጣጠራል፣አስፈላጊውንድጋፍይሰጣል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

20. በክልሉ መንግሥት ለሚከሄዱግንባታዎችዲዛይንያዘጋጃል፣የዋጋጥናትያካሂዳል፣የምህንድስናግምትያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በወለታወመሠረት መፈጸሙን ይከታተላል፣ የጥራትቁጥጥርያደርጋል፤

21. የኮንስትራክሽን ግብዓትበላቦራቶሪእየተፈተሸለግንባታአገልግሎትመዋሉን ያረጋግጣል፣

22. የክልሉንየኮንትራክሽንናየዲዛይንሥራዎችፍላጎትያጠናል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

23. አግባብ ላለው አካል በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ያወጣል፣ መከበራቸውንም ይከታተላል፤

24. የኮንስትራክሽን ዘርፍን እንቅስቃሴ ይመራል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

25. በአማካሪዎችወይምበሌላአካላትለሚሰሩዲዛይኖችየማወዳደሪያዝክረተግባርያዘጋጃል፤የአማካሪደረጃይወሰናል፣የአማካሪዎችንወርሃዊየግንባታሂደትሪፖርትይገመግማል፣የአገልግሎትክፍያቸውንያፀድቃል፤

26. በአማካሪዎችወይምበሌላአካልየተሰሩዲዛይኖችንይመረምራል፣ያፀድቃል፣የግንባታክትትልናቁጥጥርሥራዎችንያካሂዳል፣ክፍያዎችንያፀድቃል፤

27. የኮንስትራክሽንኢንዱስትሪልማትናየቁጥጥርሥራዎችንያከናወናል፤

28. የዘርፉን የሰውሀብትልማትናደረጃዎችዝግጅትሥራዎችንተግባራዊያደርጋል፣የሚመለከታቸውአካላትምያስተባብራል፤

29. በመንግስትምሆነ በግልተቋማትበህንፃአዋጁበተካተቱእናወደፊትምበሚከተቱከተሞች ለሚገነቡ ህንፃዎችዲዛይንይገመግማል፣የግንባታፈቃድእናየማጠቃሚያፈቃድይሰጣል፤

30. የህንፃሹምጽ/ቤቶችንያደራጃል፣ይመራል፣ይቆጣጠራል፣የግንባታግብአትጥናትናምርምርያካሂዳል፤ከፍተኛየትምህርትተቋማትንበጥናትናምርምርሥራወእንዲሳተፉያስተባብራል፤

31. በክልሉ የዲዛይንና የኮንስትራሽን ዘርፍ ለተሰማሩ አማካሪዎች፣ ኮንትራክተሮችእናባለሙያዎች የአቅምግንባታሥራዎችንያከናወናል፤

32. በግንባታሥራሰፊየሥራዕድልእንዲፈጠርግንባታዎችጉልበትተኮርእንዲሆኑያበረታታል፤

33. ዓላማውንለማስፈፀምየሚረዱሌሎችተግባራትንያከናወናል፡፡

## <u>አንቀጽ 17</u>

## የአስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ

ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡ -

1. በክልሉ ወስጥ ሕግና ሥርዓት ማክበሩንና የኅብረተሰቡ ደህንነት ማጠበቁን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤
2. በክልሉ ወስጥ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ አሠላካከታቸው እንዲዳብርና በሕገ - መንግስትና በሰብአዊ መብቶች ረገድ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ይሠራል፤
3. በዞን፣በልዩ ወረዳዎች ወይም በወረዳዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሠላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
4. ከአጎራባች ክልሎች ጋር በሚዋሰኑ አካባቢዎች የሚነሱ አለመግባባቶች በሠላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
5. በአስተዳደር፣በሕዝብ ደህንነትና በፀጥታሥራ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የፌደራል መንግስትና ሌሎች ክልሎችአካላት ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፤
6. ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ጥያቄ ሲቀርብ በሕግ አግባብ መሆኑን ያረጋግጣል፣ይፈቅዳል፣እንዲሁም ከተፈቀደለት ዓላማ ወጪ እንዳይሆን እና በሰላማዊ መንገድ ሚጸማ ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤
7. የሚሊሺያን የሰው ኃይል ይመለምላል፣ያሰለጥናል፣ያደራጃል፣ያስታጥቃል፣ያሰማራል ያሰናብታል፤
8. የሚሊሺያ አባላትን ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግንባታን ሥራ ከሚመለከተው አካል ጋር ያስተባብራል፤
9. ወንጀል እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ይከላከላል፣ይቆጣጠራል ከህዝባዊ ፖሊስ ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር የአካባቢ ፀጥታ ኃይል ሆኖ ይሰራል፤
10. ሚሊሺያው ከምርት ተግባሩ ሳይነጠል በአካባቢው በሚካሄደው ፀጥታ የማስከበር እንቀስቃሴዎች ከህዝባዊ ፖሊስና ከህዝብ ጋር የሚሰራበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣ይቆጣጠራል፣ለረጅም ጊዜ ከምርት ሥራ የሚነጥል የፀጥታ ሥራ እንዳይሰማሩ ይከታተላል ፣ይቆጣጠራል፤
11. ለሀገር ሠላምና ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሀገር መከላከያ ሠራዊት ጋር ይሰማራል፤
12. ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

### አንቀጽ 18

### የባህልና ቱሪዝም ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡ -

1. የሀገርቱን የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ መሠረት በማድረግበክልሉወስጥየቱሪዝም አገልግሎቶችእንዲስፋፉ ያደርጋል፤
2. በክልሉ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤ በግል ባለሃብቶች ለሚቋቋሙ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋሞች የብቃት ሚረጋገጫ ይሰጣል፣ተቋማቱ የተወሰነላቸውን ደረጃ ማጠበቃቸውን ይከታተላልይቆጣጠራል፣ የምክር አገለግሎቶችን ይሰጣል፤

3. አግባብ ካላቸው የክልሉ ማስተዳደር አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የቱሪስት ማስህቦችን ይመዝግባል፣ እንዲደራጁ፣ እንዲስፋፉ፣ እንዲለሙ እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

4. ስለ ክልሉ የቱሪዝም ማስህቦችና የቱሪዝም ልማት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀናጃል፣ ያሠራጫል፤

5. ቱሪዝም ነክ በሆኑ ጉዳዩች አግባብ ያላቸው የክልል ማስተዳደሩን አካላት ያስተባብራል፤

6. በክልሉ የሚገኙ ቅርሶችን በሚመለከት የፖሊሲ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል ይተገበራል ይከታተላል፣ ቅርሶች እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

7. የክልሉን ነባር ብሔረሰቦች ባህልና ታርክ በተመለከተ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናወናል፣ ያስተዋወቃል፣ የሚዳብሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

8. በክልሉ የባህል፣ የኪነ-ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

9. በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች እንዲተዋወቁ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲታደሱና ጥቅም ላይ እንዲወሉ ያደርጋል፤

10. ጎጂልማዳዊ ድርጊቶች ተለይተዉ እንዲታወቁ ጥናቶችን ያካሂዳል፣የሚወገዱበትን መንገድ ያመቻቻል፤

11. በክልሉ የፎቶግራፍና የስዕል ኤግዝቢሽኖች በማዘጋጀት የክልሉን ተፈጥሮአዊና ባህላዊን ቅርሶች እንዲታወቁ ያደርጋል፤

12. በዘርፉ የሚወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

13. በክልሉ ሙዚዬሞችና የህዝብ ቤተ-መጽሐፍቶች እንዲደራጁና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

14. የቱሪዝም ክፍለ ኢኮኖሚ ሥራዎች በፌደራሉና በክልሉ መንግሥት ፖሊሲዎች መሠረት መሠራቱን ይቆጣጠራል፤

15. የቱሪዝም ማስህቦችና ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ሥራ ወጤቶች እንዲታወቁ ኤግዚቢሽን ያዘጋጃል፣ በሌሎች ክልሎች በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይም ይሳተፋል፤

16. የቱሪዝምን ልማት የሚመለከቱ ጥናቶችን ያካሄዳል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ያጠናክራል፣ ለሚመለከተውክፍልያስተላልፋል፤

17. የቱሪዝም ልማት ሥራ ለማካሄድ ለሚፈለጉ የሀገር ወስጥ ባለ ሀብቶት የምክር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ሥራቸዉን ይቆጣጠራል፣ያበረታታል፤

18. የቱሪስት አገልግሎቶች ደረጃቸወን የጠበቁ መሆኑን ይቆጣጠራል፣ደረጃቸው እንዲሻሻል የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

19. የቱሪስት ማስህብነታቸው ለቱሪዝም ልማት ብቻ መዋል የሚገባቸወን ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያወላል፣ የልማት ሁኔታቸወንም ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

20. የቱሪስት መዳረሻ በሆኑ ሥፍራዎች የሚኖረው ህብረተሰብ ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያወላል፤

21. በቱሪዝም ዋና ዋና ማስህቦች አካባቢ የመሠረተ ልማት እንዲስፋፉ ጥናት ያደርጋል፣ ለሚመለከተው ክፍልያስተላልፋል፣ ወሳኔ ሲያገኝ በሥራ ላይ እንዲወል ያደርጋል፤

22. የክልሉየቱሪዝም ሀብቶች እንዲጠበቁና እንዲታወቁ የተለያዩ ማንገዶችን በማጠቀም የማስተዋወቅ ሥራ ያከናወናል፣ የአገር ወስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲያበረታታ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

23. የክልሉ የተለየ የቱሪዝም አቅም የሆነ ወን የኤኮ-ቱሪዝም መዳረሻ ልማት ላይ ያተኮረ ሥራ ይሰራል፣ከሚሞለከታቸው አካላት ጋር በመሆንም ማስህቦቹ እንዲጠበቁ የግንዛቤ ማሻሻያ ሥራዎች ያከናወናል፤

24. የሆቴሎችናየቱሪዝም ሥራ ሙሉጠኛ ተቋሞች በክልሉ የሚከፋፋበትን ስልት ይቀይሣልሥራቸወን ይቆጣጠራል፣ ይሚራል፤

25. የማሃሰቢያና የስጦታ ዕቃዎች ምርትና አቅርቦት ለሻሻል ስለሚቻልበት ሁኔታ ከሚሞለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሠራል፣የምክርና የቴክኒክ ዕገዛ ይሠራል፤

26. የቢሮወን አላሞዎች ለማስፈጸም የሚዲ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 19
## የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱ የልማት ዕቅድና ስትራቴጂ ላይ የተማከረተና በክልል ማንግስት የሚፈጸም የረዥም፣የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
2. ከሚሞለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር በረዥም በመካከለኛና በአጭር ጊዜ ዕቅዶች ወስጥ የሚፀባረቁ በክልሉ መንግስት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዳዘጋጁ ያደርጋል፣ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
3. የየሴክተሩን እቅድ አፈጻጸም እየተከታተለና እየገመገመ የተቀነባበረ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለክልሉ መንግስት ካቢኔ ያቀርባል፤
4. የክልሉ መንግስት አካላት የሀገሪቱን የፋይናንስፖሊሲዎችን፣ህጎችን፣ደንቦችንና መሚያዎችን ተከትለው ማስራታቸወን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
5. የክልሉ መንግስት ከሀገር ወስጥ ባንኮች የሚያገኘወን ብድር በክልሉ መንግስት ስም ተደራድሮ ይፈርማል፣ ብድሮችን እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፤
6. የክልል መንግስቱን የፋይናንስ ክንወን ይዞታና አስተዳደር የሚያስረዳ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልሉ ማስተዳደር ካቢኔ ያቀርባል፡፡ ለአመቱ ከተዘጋጀው በጀት ሌላ ተጨማሪ በጀት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በተገቢው አካል ሲፈቀድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡
7. ስለ ክልሉ የፋይናንስ አያያዝና አጠቃቀም ጥናት እያደረገ የመፍትሄ ሃሳብ ያመነጫል፤
8. በሌላ የክልሉ መንግስት አካል የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የክልሉ የመንግስት ሀብትና ንብረት ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል፤

9. ከክልሉ የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶችና የመንግስት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርብመደበኛና የካፒታል በጀት ትክክለኛነት እየመረመረ ዓመታዊ በጀት አጠቃሎ በማዘጋጀት ለክልሉ ማስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያስተዳድራል፤

10. የክልሉ መንግስት መ/ቤቶችግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፣ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፤

11. የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት፣ ሕዝብ፣የሳይንስና የቴክኖሎጂ ስርጭትና የአገልግሎት ሚዛኖችን ይሰበስባል፣ያጠናቅራል፣ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤

12. ለክልሉ ልማትና እድገት የሚያስፈልጉ የቅየሳ፣ የካርታና የጂኦግራፊ ጥናት ሥራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል፤

13. ስነ-ሕዝብን በሚመለከት የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች በክልሉ ወስጥ በአግባቡ ሚፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ስለአፈጻጸማቸውም ስልቶችንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሣል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም ስነ-ሕዝብን ጉዳይ እንዲሳተፉ ያስተባብራል ፣ጥናቶችንና ምርምሮችን ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

14. የክልሉን ህዝብ ልማት በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፣ይከታተላል፣ ይገመግማል ጥናቶችን ያካሂዳል ፤

15. በክልሉ ወስጥ ለመሥራት ፍላጉት ላላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መንግስታዊ በጐ አድራጊ ድርጅቶች አስፈላጊወን ትብብር በማድረግና ሚዛን በማቅረብ እንዲሁም የሚያቀርቡትን የልማት ዕቅድ በመመርመርና ተገቢወን ማስተካከያ በማድረግ ይዋዋላል፣ ያስተባብርል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፣ ከገቡት ወል ወጪ የሚንቀሳቀሱ ካሉ ተገቢወን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

16. ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር በክልሉ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጭ የሆነ አሜሌካች እቅድ ያዘጋጃል፤

17. በክልሉ እስከ ወረዳ ድረስ የሚከሄደወን የበጀት ድልደላቀመር ያዘጋጃል፣በሚመለከተው አካል ያጸድቃል፤

18. የቢሮወን አላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 20

## የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ወጣቶችበነፃ ፍላጎታቸውተደራጅተወበዲሞክራሲሥርዓትግንባታ፣ በሚልካምአስተዳደርናበልማትእንቅስቃሴእንዲሳተፉተገቢወንድጋፍያደርጋል፤
2. የወጣቶችኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችእንዲፈቱምቹሁኔታዎችንይፈጥራል፤
3. የወጣቶችንሁኔታየሚያመላክቱዝርዝርሚዛኖችንይሰበስባልያደራጃል፣ ይተነትናልበሚመለከታቸውሁሉእንዲታወቁያደርጋል፤
4. የተደራጁወጣቶችተገቢወንየቴክኒክ፣የማቴሪያልናየፋይናንስድጋፎችእንዲያገኙያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

5. ወጣቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች የ ተለያዩ አካላት የ ሚደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤
6. በገጠር እና በከተማ በስራ አጥነት የ ተጋለጡ ወጣቶች በአሜሬጭ የ ስራ መስኮች የ ሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ወጣቶችን በላቀ ደረጃ ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ጥናትና ምርምሮችን በማከናወን የ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችንና ሜቀፎችን ይቀርፃል፣ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤
7. በክልሉ የ መንግስት አካላት የ ሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የ ወጣቶች ጉዳይ እንዲካተቱ ስልት ይነ ደፋ፣ ይገ መግማል፣ ተገ ቢውን ክትትል ያደርጋል፤
8. የ ወጣቶች ስብዕና ማ ንበያ ሜከላትን እንዲገ ነ ቡ ያስተባብራል ፣ ያስፋፋል፤
9. ወጣቶች በሜልካም ስነ -ምግባር እንዲታነ ፁ ሁኔ ታዎችን ያመቻቻል፤
10. የ ወጣቶች የ በጐ ፈቃድ አገ ልግሎት ተግባር በማስደግ የ በጎነ ት አድራጎት ተግባር የ ክልሉ ባህል እንዲሆን ይሰራል፣ ያስተባብራል፤
11. የ አገ ሪቱን ስፖርት ማሰረት በሜድረግ የ አካል ማከልጠኛና ስፖርት በክልሉ ወስጥ ያስፋፋል፤
12. በክልሉ ወስጥ ለሜቋቋሙ የ ስፖርት ማህበሮች ፍቃድ ይሰጣል፣ ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
13. ክልል አቀፍ የ ስፖርት ወድድሮችን ያዘጋጃል፣ ተወዳዳሪዎችና የ ስፖርት ልዑካን አባላት በእንክብካቤ እንዲያዙና በማ ባ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፣ ሁኔ ታዎችን ያመቻቻል፤
14. ክልል አቀፍ የ ስፖርት ወድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማህበሮች መካከል የ ሚ ሳወን ክርክር ይዳኛል፣ እልባት የ ሚያገ ኝበትን ሁኔ ታ ይፈጥራል፤
15. አግባብነ ት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የ ስፖርት ትጥቅና ማሰሪያ ከአገ ር ወስጥ ወይም ከውጭ ሃገ ር የ ሚ በብትን ሁኔ ታ ያመቻቻል፤
16. ስፖርት ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ያደርጋል፣ የ ክልሉ ባህላዊ ስፖርቶች የ በለጠ እንዲታወቁ፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያደርጋል፤
17. የ ክልሉ የ ስፖርት ማህበር ገ ቢ ለታለማቸዉ አላማ ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፣ ሂሳባቸውን ይሜረምራል፣ የ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
18. በክልልና በአገ ር አቀፍ ደረጃ የ ሚያገ ለግሉ የ ስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎችን ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል ወይም አስተዳደራቸውን ይከታተላል፤
19. ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ህክምናን ያደራጃል፤
20. የ ቢሮዉን አላማዎች ለማስፈጸም የ ሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

## <u>አንቀጽ 21</u>
## <u>የ ውሃ፣ ሜድንና ኢነ ርጂ ሀብት ልማት ቢሮ</u>

ቢሮዉ የ ሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡ -

1. ስለ ውሃ ሀ ብት ጥበ ቃና አጠቃቀም የ ወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመከተል የ ክልሉን ነ ባራዊ ሁኔ ታ ያገ ናዘበ የ ሚፈጸሚያ ህጎ ችን ያመነ ጫል፤ ለተግባረዊነ ታቸው ይሰራል፣ ጣበራቸውን ያረጋግጣል፤

2. በክልሉ ወስጥ ማገኙ ሸለቆዎችን፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከምችትና ስርጭቶችን ያጠናል፣ ሚጃዎችን ይሰበስባል፣ ይማዝግባል፤ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሚከሄዱ ጥናቶች ይሳተፋል፣ በስራ ላይ ዕንዲወሉ የደርጋል፤

3. የክልሉ ውሃ ሀብት በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማከፋፈሉንና ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

4. የክልሉን የውሃ ሀብት በሚሞለከት ማንኛውንም የውሃ ሥራዎች ለማስራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፍቃድ ይሰጣል፤ ከፍተኛ ደረጃ የውሃ ሥራ ፈቃዶችን በሚኒስቴር ማስሪያ ቤት እንዲሰጡ ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፤

5. የክልሉን የውሃ ክፍያ ታሪፍ በተማለከተ ጥናቶች ያካሂዳል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ያቆጣጠራል፤

6. ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ለሚውል ውሃ የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ በተወሰነወም የጥራት ደረጃ ማሰረት ፍሳሾች የተወሰነወን የጠፍማነት ደረጃ በክልሉ ወስጥ በሥራ ለይ መዋሉን የከታተላል ይቆጣጠራል፤

7. ከማዕከል የሚኒስቴር መ/ቤት ጋር በመመያየት የውሃ ሀብት አጠቃቀምን ይወስናል፤ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ በሥራ ይተገብራል፤

8. በክልሉ በውሃ ሥራ ላይ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይተባበራል፤የሥራ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

9. የሜቱሮሎጂና የኃይድሮ ጂኦሎጂ ሚጃዎችን በማስብሰብ ረገድ ከሚሞለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ ሚጃዎችን ለቀጣይ ጥናት ያደራጃል፤

10. የውሃ ሀብት ልማት ጥናቶችን ያካሄዳል፣ዲዛይኖችን ይሠራል፣ ሚጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣በሥራ ላይ እንዲወሉ ያደርጋል፤

11. ንፁህ የማጠጥ ወሃ በክልሉ ከተሞችና የገጠር ሕብረተሰብ የሚዳረስበትን ሁኔታያመቻቻል፣ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ አቅም በፈቀደ ማጠን ለቤት እንስሳት የማጠጥ ወሃ አቅርቦትን ያመቻቻል፤

12. የክልሉ ሕብረተሰብና ባለሀብቶች በወሃ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ ተገቢውን የሞያና የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፤ በክልል ደረጃ የሚሠሩ የውሃ ሥራዎች ፈቃድ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

13. የማጠጥ ወሃ ተቋሞችን የእንክብካቤ ማጠን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በወሃ ልገሳቸው አቅም ላይ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱ ወጤት ላይ የተማሰረተ መፍትሔ ይሰጣል፤

14. በሴክተሩ ለሚሠሩ ተቋማትና ባለሞያዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናወናል፤

15. በሴክተሩ ለወረዳዎች፣ ለዞኖችና በወሃ ሥራ ላይ ለተሠማሩ አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ይከታተለል፣ይቆጣጠራል፤

16. ለማዕድንና ኢነርጂ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በማከተል የክልሉነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ ሕጎችን ያመነጫል፣ ያወጣል፤ የወጡትንም በክልሉ ወስጥ ማከበራቸውን ያረጋግጣል፤

17. የማዕድን ሀብትን በማጠበቅ ረገድ ከማዕድንና ኢነርጂ ሚንስቴር ጋር በመተባበር ይሠራል፤ በክልሉ ወስጥ ለሚከሄደው የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ የልማት ፈቃድ ያወጣል፤

18. በክልሉ የሚገኙ ለማስና ልማት ሊወሉ የሚችሉ ማንኛውም እምቅ የውሃ ሀብት ያጠናል፣ ለማስና ልማት እንዲወሉ ያደርጋል፤

19. በክልሉ የሚገኙ ማንኛውንም የውሃ ሀብት ያስተዳድራል፣ ለልማት እንዲወሉ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

20. ውሃ ነክ ጉዳዩች የማማከር፣ የውሃ ሥራ ፈቃድና ሞያዊ ሚ.ጋገጫ የምሥክር ወረቀት ይሠጣል፤

21. በክልሉ ወስጥ ለሚከሄዱ የውሃ ሥራዎች የቁፋሮ ደረጃዎች ያወጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ሥራውም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የወጡ ሕጎችን የተከተለ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

22. በክልሉ ወስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለማዳረስ በነዳጅ ኃይል የሚሠሩ አነስተኛ የውሃ ኃይል ማምንጫ ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ ስፈቀደም በሥራ ላይ እንዲወል ያደርጋል፣ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይልና ታዳሽ ኃይሎች የማማንጩትና የማሰራጩት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

23. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የሚያስፈልገውን ጋዝ፣ነዳጅና የነዳጅ ወጤቶች የሚቀርቡበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ የተወሰነ ኢነርጂ ማጠበበቂያ ክምችት እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፤

24. ባህላዊ ማዕድን ማምረቻ ሥራዎችን ያበረታታል፣የኮንስትራክሽን ማዕድን፣የከበሩ ማዕድናት የፍለጋ፣ የምርመራ፣ የማምረት ሥራና የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል፡፡

25. የቢሮውን አላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎችተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 22

## የጤና ጥበቃ ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ ማስረት በማድረግ የክልሉ ህዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል ሲፈቀደም በሥራ ላይ ያወላል፤

2. ስለህዝቡ ጤና አጠባበቅ የሚወጡ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ወስጥ ማከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ደንቦችና መመያዎች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

3. በክልሉ ወስጥ በሚቋቋሙ ሆስፒታሎች፣ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች የምርምር የማሰልጠኛ ተቋሞችን ያደራጃል ያስተዳድራል፤

4. በሀገር ወስጥ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለሚቋቋም የጤና ጣቢያዎች፣የክሊኒኮች የላቦራቶሪዎችና የፋርማሲዎች ፈቃድ ይሰጣል በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን ደረጃ ጠበቀው ማሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤

5. በክልሉ ወስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሞያዎች የተወሰነውን ደረጃማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፤

6. ፍቱንነታቸውን የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶችን የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ ህክምና ጋር ተዋህደው ሥራ ላይ እንዲወሉ ያደርጋል፣የምዝገባ ደንብና ስርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

7. ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት ክትባቶች እንዲሰጡ ሌሎች ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

8. የህዝቡን ጤና ለማጠበቅ በሚደረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ይሳተፋል፣ በጠረፍ አካባቢ እንዲቋቋሙ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤

9. የምግቦችንና ማጠጦችን ለጤና ተስማሚነት ያረጋግጣል፣ የአገልግሎት ሰጭ ተቋሞችን የንፅህና አያያዝ ይቆጣጠራል፤

10. የጤና ፖሊሲውን ማስረት አድርጐ ህዝቡ በበሽታ መከላከል ላይ በስፋት የሚሳተፉበትን፣ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤

11. ስለሥራው አፈጻጸም ወቅታዊ ሚጃዎችን እያዘጋጀ ለክልሉ ማስተዳድርና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

12. በክልል ወስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

13. በጤና ዘርፍ በሁሉም ደረጃዎች ለሚገኙ የጤና ሠራተኞች አስተዳዳሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሀይሎች ከጤና አገልግሎቱ ዓላማዎች አቅጣጫ ተገቢና ተከታታይ ሥልጠና ይሰጣል፤

14. በጤና አገልግሎት ሥርዓት በሁሉም ደረጃዎች የሚያስፈልጉና ደረጃቸውን የጠበቁ መድኃኒቶችና መሣሪያዎች አቅርቦት በየጊዜው ያሻሽላል፤

15. መድሃኒቶችን፣ የክትባት መገልገያዎችን፣ የክሕምና ቁሳቁሶችን፣ መሣሪያዎችን በየአይነታቸውና እንደ አስፈላጊነታቸው ለጤና ተቋማት አቅርቦት ያሳድጋል፡፡ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ማላዋወጫ አቅርቦት ጥገናና እንክብካቤ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

16. በዋና ዋና የጤና ችግሮችና የጤና አገልግሎት ሥርዓቶች ተግባራዊ ምርምር ያስፋፋል፤

17. የተለመዱ የሕፃናት በሽታዎችን በተለይ የተቅማጥ የመተንፈሻ አካላት ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ባሉት የጤና መገልገያዎች በወቅቱ ማጠቀምና የወጣቶች ልዩ የጤና ችግሮች ከዕድሜያቸው ጋር የተያያዙ የጤና ፍላጐቶች ላይ ትኩረት ማድረግ፤

18. አግባብ ያለው የሥራ ፈቃድ በማስጠት የግል የሕክምና ድርጅቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

19. በክልሉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ህዝባዊና ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል ግንኙነት ያደርጋል፤

20. የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂክ ፕላን፣ እንዲሁም የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፀድቁም በሥራ ላይ ያወላል፤

21. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ገንዘብና የተለያዩ ዕርዳታዎችን ያሰባስባል፤

22. በክልሉ የሚከናወኑ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የአባላዘር በሽታዎችን ቁጥጥር ሪፖርት ያጠናክራል፣ በአግባቡ ተንትኖ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

23. በክልሉ ወስጥ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ የሚደረጉ ጥናቶችን ያበረታታል፣ የተገኙትን ወጤቶችም ከፖሊሲው አኳያ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

24. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስሜልከቶ የጠና አጠባበቅ ትምህርት በህብረተሰቡ በስፋትና በጥራት የሚደረስበትን ማንገድ ይቀይሳል፣ የትምህርት ሚርጃ መሣሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ በቅንጅት ተግባራዊ ያደርጋል፤

25. ዓላማውንለማስፈፀምየሚዳሉሎችተግባራትንያከናውናል፤

## አንቀጽ 23

## ፍትህ ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡ –

1. የሕግ ጉዳዮችን በሚሞለከት የክልሉ ማንግስት አማካሪ ሆኖ ይሰራል፤
2. የክልሉን ዐቃቤ ህግ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
3. በሌሎች ህጎች ለሌሎች አካላት የተሠጠ የወንጀል ሥልጣን እነደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ወንጀሎች የክልሉን ማንግስት በመወከል ይከራከራል፤
4. ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ በሕጉ መሠረት አጥፊዎችን ተከታትሎ በማያዝ በአጥፊዎች ላይ የወንጀል ምርመራ ያካሂዳል፣በሕጉ መሠረት ለፍርድ ቀርበው ተገቢውን ወሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
5. በማረሚያ ቤት፣በማረፊያ ቤት፣በፀባይ ማረሚያና ጊዜያዊ የእስረኞች ማጠለያ የሚገኙ ሰዎች በአግባቡ መያዛቸውንና ህጋዊ መብታቸው መከበሩን ያረጋግጣል፤
6. በክልሉ ማንግስት ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፣ በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ ያነሳል፤
7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል ማስኤዎችን ያጠናል፣ለወንጀል መከላከል የሚረዱ ጥናቶች ያካሂዳል፣ወንጀል የሚቀንስበትን ስልት ይቀይሳል፤
8. ለወንጀል ድርጊት ምስክሮች እንደአስፈላጊነቱ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
9. በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በክልሉ ፍ/ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች ካሳ እንዲያገኙ በፍትሀብሔር ክስ ይረዳል፤
10. የእያንዳንዱ መ/ቤት የማንግስትና የህዝብ መብትና ጥቅም የማስከበር ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝቡን እንዲሁም የክልሉን ማንግስት መብትና ጥቅም ለማስከበር በፌደራልና በክልሉ ፍ/ቤቶች በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክስ ይመሰረታል፣ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል፣ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፤
11. የክልሉ ማንግስት ወይም አካላቱ ተከራካሪ የሚሆኑባቸውን የፍትሐብሄር የመብት ጥያቄዎችን አያያዝ እንደአስፈላጊነቱ ይከታተላል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፣ ለዚህም ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፤
12. በክልሉ ማንግስት ወይም በአካላቱ ጥያቄ ሲቀርብለት የህግና ደንቦች ረቂቅ በማዘጋጀት ይረዳል፤

13. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትርፍ ላይ ያልተመሠረተ ዓላማ ይዘው የተቋቋመ በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራትን ይመዘግባል፣ፈቃድ ይሰጣል፤

14. በክልሉ ማኅግስት ፍ/ቤቶች ለመከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፍቃድይሰጣል፣ይሰርዛል፤ዲስፐሊን ጉዳይ ያያል፤

15. ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ አንፃር የህዝብን ንቃተ-ህግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የህግ ትምህርት ይሰጣል፤

16. የክልሉን ሕጎች የማጠቃለል ስራ ያካሂዳል፤

17. በክልሉ ውስጥ የሰነድ ሚረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ይሰጣል፣ ሰነድ ይሰርዛል፣ይሽራል፣አስፈላጊ ሲሆን እንዲደራጅ ያደርጋል፤

18. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ ዳኞች፣ዐቃብያን ሕግ፣ለፖሊስ ሌሎች አሚራር አካላት እንደአስፈላጊነቱ የሥልጠና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ሥልጠናም ይሰጣል፤

19. ለባህላዊና ልማዳዊ የዳኝነት አካላት አስፈላጊውን ስልጠና ይሰጣል፤

20. የክልሉ የፍትህ አስተዳደርና አገልግሎት ሥርዓት የሚሻሻልበትን መንገድ ያጠናል፣በአግባቡ ተደራጅቶ ለክልሉ ሕብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

21. ዓላማውንለማስፈፀምየሚዳሉሌችተግባራትንያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 24

## የትምህርት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንናተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ማስረት የክልሉን የትምህርት ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

2. በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር ዕድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣መሠረታዊ ትምህርትን ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፤

3. የክልሉ የትምህርትጥራት በአገር አቀፍ ደረጃ የተወሰነለትን ስታንደርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

4. የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና ስታንዳርድ ተከትሎና የክልሉንና የአካባቢውን ሁኔታዎች በማገናዘብ የክልሉን አንደኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ይተገብራል፣እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር የሚዘጋጀውን የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ሥራ ላይ ያውላል፤

5. በደረጃው ለሚስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ መምህራንንና የትምህርት ባለሞያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑም ያደርጋል፤

6. የመጀመሪያ ትምህርትን በነባር ብሄረሰቦች አፍ መፍቻ ቋንቋ ለመስጠት ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ይተገብራል፤

7. በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ት/ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎችን ተከታትሎ ያስፈጽማል፣በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣የምስክር ወረቀቶችንብቃት ያረጋግጣል፤

8. ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ የመጫያና ማስተማሪያ መፃህፍትና ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ማጣቀሻ መጽሐፍት እንዲሁም ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

9. በክልሉ የሚገኙትን የትምህርት ተቋማትን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣ይከታተላል፣ እገዛ ይሰጣል፤

10. በክልሉ የትምህርት ተቋማትን ግንባታ ያካሂዳል፣ ያደራጃል፤ ደህንነታቸውን ይከታተላል፤

11. የክልሉን የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ኮሌጆችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤

12. በድርጅቶችና ባለሀብቶች ለሚቋቋሙ እስከ ኮሌጅ ደረጃ ላሉ የትምህርት ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

13. ለትምህርት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

14. ለክልሉ ነባር ብሔረሰቦች፣ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ልዩ ፍልጎት ትምህርት ለሚሹና ለጉልማሶች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፤

15. የክልሉ ትምህርት ፕሮግራም በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ያደርጋል፤

16. የትምህርቱን ሥራ ማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

17. የትምህርት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ያጠናቅራል፣ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤

18. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ህብረተሰቡንና መያዶችን ሊያሳትፍ የሚችል ስልት ይቀይሳል፣ያስተባብራል፤

19. ከትምህርት ሥራ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ጉዳዮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትአብሮ ይሠራል፤

20. ዓላማውንለማስፈፀምየሚዳሌሎችተግባራትንያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 25

## የሴቶች እናህፃናት ጉዳይ ቢሮ

ቢሮውየሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡ -

1. የሴቶችናሕፃናትመብትናጥቅሞችንበማስከበርዙሪያግንዛቤናንቅናቄእንዲፈጠርያደርጋል፤
2. ሴቶችበክልሉየኢኮኖሚ ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ወስጥ በንቃት ለመሳተፍየሚያስችላቸውዕድሎችየተመቻቹላቸውመሆኑን ያረጋግጣል፤
3. ሴቶች እንደየፍላጎቶቻቸዉና እንደ ችግሮቻቸውተደራጅተውለመብቶቻቸውእንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድእንዲችሉያበረታታል፣ሁኔታዎችንያመቻቻል፤
4. በክልሉመንግስትአካላትየሚዘጋጁፖሊሲዎች፣ሕጎች፣የልማትፕሮግራሞችናፕሮጀክቶችየሴቶችናሕጻናትጉዳይእንዲያካትቱ ስልትይነድፋል፣ይገመግማል፣ተገቢውንክትትልያደርጋል፤

5. በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀመመድሎዎችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችንበጥናት በማየት የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻፀሙ ይከታተላል፣ ግንዛቤየማስጨበጥስራይሰራል፤

6. በክልል ደረጃ የሴቶች የልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙም ይከታተላል፤

7. ሴቶችበተለያዩየመንግስትአካላትበወሳኔሰጪስራቦታዎችላይለመመደብበቂትኩረትየተሰጣቸውመሆኑንያረጋግጣል፤

8. በዝቅተኛየኑሮደረጃላይየሚገኙሴቶችንየኑሮሁኔታለማሻሻልየሚዱጥናቶችንያካሂዳል፣ ፕሮግራሞችናፕሮጀክቶችንበመቅረፅተግባራዊእንዲሆኑያደርጋል፣ የብድርናቁጠባአገልግሎትየሚገኙበትንሁኔታእንዲመቻች ያደርጋል፣ አፈጻፀሙይከታተላል፤

9. የሴቶችአደረጃጀቶችንአቅምለማጎልበትየሚያስችሉጥናቶችንያካሂዳል፣ ስልጠናዎችንይሰጣል፣ የስልጠናአገልግሎትየሚሰጥበትንአሰራርያመቻቻል፣ ያስተባብራል፤

10. የእናቶችየኑሮሁኔታስለሚሻሻልበትናየሕፃናትመብትናደህንነትስለሚጠበቅበትሁኔታያጠናልከሚመለከታቸውአካላትጋርበመተባበርተግባራዊያደርጋል፤

11. ሴቶችንናሕጻናትንየሚመለከቱሀገራችንየፈረመቻቸውዓለምአቀፍወሎችናስምምነቶችአፈጻፀምይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትምሪፖርትያቀርባል፤

12. ዓላማውንተግባራዊለማድረግየሚያስፈልጉሌሎችተግባራትንያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 26

## የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. ለመንግሥት የኮሚኒኬሽን ሥራ አመራር ማስጠትና በማስኩ ሜልካም አፈጻጸምየሚኖርበትን ሥርዓት መፍጠር ፤

2. ለክልል መንግሥት ማሥሪያ ቤቶች የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አቅጣጫ ማስቀመጥና ማስተባበር ፤

3. የክልል መንግሥት ማሥሪያ ቤቶች የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኞችን የአቅም ግንባታ ተግባሮች ማከናወን፣አጠቃላይ የስምሪትና የእድገት አቅጣጫ መወሰን ፤

4. የመንግሥት ቃል አቀባይነት ሥራን ጨምሮ የመንግሥት ኢንፎርሜሽን ዋነኛ ምንጭ በመሆን ማገልገል፣የመንግሥትን መልዕክቶች መቅረጽና በልዩ ልዩ መንገዶች ማሰራጨት፣በሀገራዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዩች ላይ የመንግሥትን አቋም መግለጽ ፤

5. የመንግሥት የኮሚኒኬሽን ፕሮግራሞችን ይዘትና አፈጻጸም ማቀናጀት ፤

6. የሀገር ወስጥና የውጭ የክልል ሚዲያ የዕለት ተዕለት ዘገባ ቅኝት ሥራዎችን በማከናወንና የሕዝብ አስተያየት በማሰባሰብ መተንተንና ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፤

7. በመንግሥት ፖሊሲዎችና በተለያዩ ሃገራዊ ጉዳዩች ላይ ግንዛቤ ለማስጠትና ግልጽነትን ለመፍጠር ሕዝባዊ የወይይት መድረኮችን ማዘጋጀትና ማስተባበር ፤

24. **የክልሉን የአካባቢ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መረጃዎችን ለማደራጀት ስርዓት ይዘረጋል፣** ክልላዊየ ሚጃቋትይጣርታል፣ **መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ትንተና እያካሄደ** ወቅታዊማተካከያዎችንያደርጋል፣ በአካባቢናበተፈጥሮሀብትልማት ዘርፍፍላጎትላላቸው **ተጠቃሚዎች** ዝግጁያደርጋልያሰራጫል፤

25. የክልሉ የልማት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ዘላቂ የሜሬት አጠቃቀምን ማሰረት አድርገዉ እንዲተገበሩ ክልል አቀፍ ሜ የሜሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፤

26. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሠረት ወል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

27. ዓላማውን ለማከፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 28</u>

## <u>ገቢዎች ባለስልጣን</u>

ባለስልጣን ማሰሪያቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡-

1. በክልሉ ወስጥ የታክስ ሕጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን ያስከብራል፣ ያስፈጽማል፤
2. በህግ ተለይተው በክልሉ መንግስት እንዲሰበሰቡ የተመደቡትንና ከፌደራሉ መንግስት በሚሰጠው ወክልና መሠረት በክልሉ መንግስት እወቅና የፌዴራልንና የጋራ ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤
3. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመሥርቶ ጥናቶችን በማካሄድ የክልሉን የገቢ መሠረት ያሰፋል፤ በታክስ አስተዳደሩ የሚከሰቱ ችግሮችን በማጥናት እንዲፈቱ ያደርጋል፤
4. በክልሉ ወስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አፈፃፀም በባለቤትነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
5. የታክስ ሕጎችን ለማከፈፀም የሚያስፈልጉትንና በማቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፤
6. ታክስ ከፋዩ ህብረተሰብ ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን እንዲያዳብርና መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ እንዲረዳ በተለያዩ የግንዛቤ ማከጨጫ ሚድረኮች ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የታክስ አስተዳደር ብቃት ያላቸውን ባለሙዎች ለማፍራት የሚያስችለውን የስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስልቶች ይዘረጋል፤
7. የታክስ ህጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፣ ይከሳል፣ ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቢያነ-ህግና የታክስ ወንጀል መርማሪዎች ያደራጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤
8. በክልሉ ወስጥ ዘመናዊ የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ስርዓት በማዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤ በማስኩ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ታክስ ነክ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤
9. በክልሉ ወስጥ ለሚገኙት ታዳጊ ከተሞች እና ማዘጋጃ ቤቶች ለሚሰበሰቧቸው ገቢዎች ባለስልጣኑ ሁሉአቀፍ የሙያ ድጋፍ እና የተሟላ አቅም እንዲኖራቸው የአሰራር ስልጠና፤ ክትትልናድጋፍ ይሰጣል፡
10. ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉትን ሚጃዎች ያሰባስባል፤ ያጠናክራል፤ እነዚህኑ በማጠቀም ታክስ ይወስናል፤ ይሰበስባል፤ የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣትና ማሻሻል ሲያስፈልግ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለክልሉ መንግስት አቅርቦ ያስወስናል፤

11. ለታክስ ከፋዩ አሚራጭ የታክስ ጣከፈያ ተቋማትን ያማቻቻል፤

12. የሥራያ ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤ የስራ እንቅስቃሴዎቹን በሚመለከት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርቶችን ያቀርባል፤

13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተደረገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ወንጀሎችን የመመርመርና የመክሰስ ስልጣኑን እንደአስፈላጊነቱ ለክልሉ ፖሊስ እና ለክልሉ ፍትህ አካላትበወክልና ለሰጥና ሊያሰራ ይችላል፤

14. ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ በክልሉ ማስተዳደር ም/ቤት ጸደቆ በሚወጣ ልዩ የባለስልጣኑ የሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤ያሰናብታል፡፡

15. ባለስልጣኑ በክልሉማንግሥትና በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ስልጣን ሥር የሚወድቁትንና የጋራ የግብር እና ታክስ መሠረቶችን አይነትና ብዛት ይለያል፤ በእነዚሁ አካላት መካከል የሚከፋፈልበትን ቀመር ያዘጋጃል፣ ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፤

16. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፤

17. ዓላማዎችን ለማስፈጸም የሚዳሉሉች በህግ የተፈቀደ ተግባራትን ያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 29

## የቴክኒክ ሙያና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የሀገሪቱንየቴክኒክናሙያትምህርትናስልጠናስትራቴጂናመርሀ-ግብርበክልልደረጃለማስፈፀምየሚያስችሉወቅታዊእቅዶችንያዘጋጃል፣የቴክኒክናሙያትምህርትናስልጠናየሚያንለብ ቱፕሮጀክቶችንያዘጋጃል ሲፀድቁም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
2. በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡየቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሙያ ደረጃዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
3. በሚወጣው አገር አቀፍ መመዘኛ መሰረት የመካከለኛ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች በክልሉ ወስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤
4. በኤጀንሲው የሚዘጋጁ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓተ-ትምህርቶች በክልሉ ወስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ፡-
   (ሀ) መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ/አጫጭር/ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎችን በሚመለከት ስርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ያደርጋል፣ይቆጣጠራል፡፡
   (ለ) በክልሉ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አጥንተው በሚያቀርቡት የወሳኔ ሃሳብ መሰረት አዳዲስ የስልጠና ማስኮች ለመክፈት ሲፈልጉ ኤጀንሲው እንዲከፍቱ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
5. የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲመሩባቸው የወጠና/ወይም የሚወጡ መመዘኛዎች በክልሉ ወስጥ በሚገኙና የሚቋቋሙ የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣እንዲሁም የማሰልጠኛ ተቋማትን

እውቅና አሰጣጥ በሚመለከት የሚወጡ አገር አቀፍና የክልሉ መመሪያዎችን በክልሉ ወስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፤

6. በክልሉ ወስጥ የሚከሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎች የሙያ ብቃት ምዘናና ሚረጋገጫ ሚከልን ያደራጃል፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ክህሎት ምዝና አፈጻጸም መቆጣጠርን ጨምሮ በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጥራት መኖሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

7. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ሚከላት እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፡፡

8. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥንበሚመለከት የሚወጣው አገር አቀፍ መመሪያ በክልሉ ወስጥ በሚከሄዱ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፣

9. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከማምረቻና ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው የሥራ ላይ ልምምድ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፡፡

10. በክልሉ ወስጥ የሚከሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ከክልሉ ማንግስት የልማት ትልምና የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር በተጣጣመ ሚልኩ መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ከክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ለሚድረግ የሚያስችሉ የሙያ ገበያ ፍላጎትና ሌሎችንም ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ያስተዋወቃል፣ የጥናትና ምርምር ወጤቶች ቤተ-መፃ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ክፍት ያደርጋል፣

11. በክልሉ ወስጥ የሚከሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ወጤታማነት ለሚረጋገጥ እንዲቻል የደህረ ስልጠና ክትትልያደርጋል የደህረ ሥልጠና ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣

12. በክልሉ ወስጥ በሚከሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በዚህ ረገድ የሚቀየሱ አገር አቀፍ ስርዓቶች በክልሉ ወስጥ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣

13. በክልሉ ወስጥ ለሚከሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የደረጃ ብቃት ሚረጋገጫ የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በሚወጣው ደንብ መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑትንና የሥልጠና ጥራት ላይ ችግር ያለባቸውን ተቋማት የዕወቅና ፈቃድ ይሰርዛል፤

14. የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፣ እንዲሁም ቦርዶች በክልሉ ኮሌጆችና በተቋማት ደረጃ በህግ መሠረት መቋቋማቸውን ይከታተላል አደረጃጀታቸውና አስተዳደራቸውን እያጠና እንዲሻሻል ለሚመለከተው ያቀርባል፣ የሥልጠና አካሄዳቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

15. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የምርት ሚከላትን በሚቋቋምና የገቢ ማዳበሪያ ሥርዓት በማዝርጋት የወስጥ ገቢያቸውን የሚያዳብሩባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

16. የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን በሙያቸው ተደራጅተው ወደ ሥራ በሚገቡበት ያላቸውን የሙያ ክፍተት በማየት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት በየደረጃው ሙያዊ እገዛ እንዲደረግላቸው አስፈላጊውን የሥራ ትብብር ያደርጋል እገዛ መደረጉን ይከታተላል፤

17. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፤

18. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የለውጥ ሥራዎች ላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚሰለጥኑ ባለሙያዎች የጨበጡትን ዕውቀት ለሚመለከታቸው ፈፃሚ ባለድርሻዎች ማስተላለፋቸውን ይከታተላል፤

19. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የግል ባለሀብቶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ጋር የጠነከረ ግንኙነት ይዘረጋል፣ ያበረታታል፣ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

20. በክልሉ ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ስርጭት የተመጣጠነ መሆኑን ይከታተላል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ተጨማሪ ተቋማት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል የሥልጠናዎችን ጥራትና ብቃት ያረጋግጣል ይቆጣጠራል፤

21. በክልሉ ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እንዲሁም ከሀገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ መሰል ተቋማት ጋር ግንኙነትን በመፍጠር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፣ የጋራ ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይፈራረማል፤

22. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና ተቋማት ከተለያዩ መንግሥታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር ሥልጠና እንዲፈራረሙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ይከታተላል፤

23. ከትምህርት ስርዓቱ ጋር የተጣጣመ አፈጻጸም እንዲኖር ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፣ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለሀገር አቀፍ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ እስትራቴጂዎችና መርሃግብሮች የተቀናጀ አፈጻጸም የክልሉን ድርሻ በሚመለከት ከአገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ጋር እንደየአግባቡ ተቀናጅቶ ይሰራል፣

24. የዘርፉን የልማት ስትራቴጂ በተገቢው ሁኔታ መተግበሩን ማረጋገጥ፣ በስትራቴጂው አፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን መፍታት፤

25. የዘርፉን ልማት **ለማፋጠን** የተዘጋጁ የድጋፍ ማዕቀፎች፣ የአቅም ግንባታ መርሀ ግብሮችና እነዚህኑ ለማስፈፀም የተዘጋጁ **ረቂቅ** መመሪያዎችን መነሻ በማድረግና**በማጣጣም** **አፀ□ቆ** ተግባራዊ **ማ□ረ□**፣

26. በዘርፉ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች **በ**ቂየማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች **መ□□□ታቸውንና** በግልፅ መመሪያ **መተላለፋቸውን** ማረጋገጥ፤

41. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመከሰስና የመክሰስ፤

42. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## የአስፈፃሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች መዋቅር እና ኃላፊዎች

### አንቀጽ 30

### የአስፈፃሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆኑ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች እንደሁኔታው በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ተሻሽለወእንደገና ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በማስተዳድር ም/ቤቱ ይወሰናል፤
2. የአስተዳደር ምክር ቤት አባል የሆኑ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የአስፈፃሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች ተጠሪነት ለዋና አስተዳዳሪወና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ እንዲሁም በየደረጃው ላሉ የአስፈፃሚ አካላት ማስሪያ ቤቶች ይሆናል፤
3. ለአስፈፃሚ የመንግስትማሥሪያቤቶችየተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በየአስተዳደር እርከን ላሉት ማስሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚ ይሆናል፤
4. እያንዳንዱ የአስፈፃሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች፤ እንዲሁም የሥራ ሂደት ባለቤቶች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፤
5. ተቀራራቢ ተግባር ያላቸው የአስፈፃሚ አካላት ማሥሪያ ቤቶች አንድ የድጋፍ ሰጪ ሜከል በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤
6. በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ ማሥሪያ ቤቶች በየአስተዳደር እርከኑ እንደ አስፈላጊነቱ ተቀናጅተው ወይም ተጣምረው ሊደራጁ ይችላሉ፤

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 31

### አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለሚደራጀት

የማስተዳደር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት፣ ማንኛውም አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ ወይም ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈልወይም ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥወይም አዲስ አስፈጻሚ አካል እንዲቋቋም በሚድረግ የክልሉን መንግሥትአስፈጻሚአካላት ማስሪያ ቤቶችን የሚደራጀት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

### አንቀጽ 32

## ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን ማስተዳደር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፤
2. ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን የማስተዳደር ምክር ቤት አባል የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት ማስፈያቤቶች ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 33

## የተሻሩ ሕጎች

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 94/2003ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
2. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 94/2003 ዓ/ም በከፊል ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 118/2005 ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
3. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ኮሚኬሽን ቢሮን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 101/2003 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
4. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 102/2004 ዓ.ም ማቋቋምንና ዝርዝር ተግባራትን በተመለከተ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
5. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ጽህፈት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 30/1995 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
6. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የሚሊሻ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 88/2002 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
7. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 34

## መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ

1. የወጣቶችንጉዳዩችየሚመለከቱ የቀድሞ የሴቶች፣ሕፃናት እና ወጣቶችጉዳይቢሮ መብትናግዴታዎችበዚህአዋጅለወጣቶችናስፖርትቢሮ ተላልፈዋል፤
2. የደን ልማትና ጥበቃ ዘርፍንየሚመለከቱ የቀድሞ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ መብትናግዴታዎችበዚህአዋጅለአካባቢ፣ ደንናየሜት አስተዳደር ቢሮ ተላልፈዋል፤
3. ስለ ሚሊሻ ጉዳይ የሚመለከቱ የቀድሞ የሚሊሻ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ተላልፈዋል፤

4. የኤች አይቪን ጉዳይ የሚሟከቱ የቀደሞው የኤችአይቪ ኤድስ ማካላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ጽህፈት ቤትመብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጤና ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

5. የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ማስረት ለቴክኒክ ሙያናአነስተኛኢንተርፕራይዞች ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

6. አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ግብይት በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የነበረዉ በዚህ አዋጅ ማስረት ለንግድ፣ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

## አንቀጽ 35

## አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤትከፀደቀበት ማስከረም/2008 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

አሶሳ

ማስከረም 2008 ዓ/ም